አምሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፯
53rd Year — No. 77

አዲስ አበባ መጋቢት ፭ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም.
Addis Ababa, 14th March 1994.

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

# ነጋሪት ጋዜጣ
# NEGARIT GAZETA

OF THE TRANSITIONAL GOVERNMENT OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ Unit Price 1.20 | በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁ. ፹ሺ፩ (80,001) |

ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፹፮ ዓ. ም.**

የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ . . . . . . . . . . . . . ገጽ ፫፻፶፯

ማረሚያ ቁጥር ፰/፲፱፻፹፮ . . . . . . ገጽ ፫፻፷፫

ማረሚያ ቁጥር ፱/፲፱፻፹፮ . . . . . . ገጽ ፫፻፷፫

## አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፹፮

## የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ፡

ኢትዮጵያ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች በተለይም በግብርና ፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ምርታማነትን በማሳደግ የሕዝቦችን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት የምታደርገው ሁለገብ ጥረት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መታገዝ ያለበት በመሆኑ ፤

በአገሪቱ ከሚከናወኑት የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለብሔራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚኖራቸውን መርጦ መደገፍና ማበረታታት እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥገኝነትን በመቀነስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን መገንባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በአጠቃላይም ብሔራዊውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም በስፋትና በጥራት ለማዳበርና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስክ የሚደረገውን እንቅስቃሴና ጥረት በስርዓት ለመምራትና ለማስተባበር የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽንን እንደገና ማቋቋም በማስፈለጉ ፤

በሽግግሩ ወቅት ቻርተር አንቀጽ ፱ (መ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል ።

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፹፯» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## ፪. መቋቋም

፩. የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ( ከዚህ በኋላ «ኮሚሽን» እየተባለ የሚጠራ ) እራሱን የቻለ የማዕከላዊ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፪. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል ።

## ፫. ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሀገሪቱ ውስጥ በማናቸውም ቦታ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል ።

## ፬. አላማ

የኮሚሽኑ አላማ

፩. የሀገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን ማበረታታት ፣ ማገልበትና መርዳት ፤

፪. ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለማጎልበት በሚያስችል ብሔራዊ አቅም መገንባት ፣

፫. የሕዝቡን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግንዛቤ ዕውቀትና ባህል እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን የመጠቀም ልምድን ማሻሻልና ማዳበር፤

፬. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስርዓት ይበልጥ ውጤታማ ፣ ቀልጣፋና በልማት ላይ ያተኮረ ማድረግ ፣

## ፭. ስልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

፩. የሀገሪቱን የዕድገት አላማዎች ተግባራዊነት የሚያግዝ ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ መንደፍና በማዕከላዊ መንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል ፤

፪. ሁለገብ የሆኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕቅዶችን ማቀድና የዘርፍ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎች ፣ ዕቅዶች ፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ መመሪያ መስጠት ተዘጋጅተው ሲቀርቡም መገምገምና በመመሪያው መሰረት መዘጋጀቱን ማረጋገጥ ለመንግስት አቅርቦ ማስፀደቅ ፤

፫. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ በአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት እስከ ፩ ነጥብ ፭ በመቶ የሚደርስ በጀት እንዲመደብ ማድረግ የተመደበ በጀትን ስርጭትና አጠቃቀም መከታተል፤ በተጨማሪም የፋይናንስ ሪፖርት መቀበል ፤

፬. በተለያዩ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፎች ወስጥ ምርምርና ስርፀት የሚያከናውኑና ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት አስተዋፅኦ የሚኖራቸው ማዕከላትና ተቋማት በማዕከልና በክልል ወይም በአገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚደራጁበትን መንገድ ማመቻቸት፤ መርዳትና ማበረታታት ፤

፭. ጠቀሜታና ተግባራዊ ብቃት ያላቸው የምርምርና ስርፀት ውጤቶች በኅብረተሰቡ ዘንድ እንዲታወቁና በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ውስጥ እንዲሰርጹ ማድረግ ፤

፮. ገበሬውና የገጠሩ ሕዝብ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚረዳበትን መንገድ ማመቻቸት ፤

፯. ሴቶችና ወጣቶች በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ከፍ እንዲል ማበረታታት ፣ መርዳት ፤

፰. የኅብረተሰቡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግንዛቤ እንዲጐለብት አመች በሆኑ የማሰራጫ ዘዴዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ አህዛቦት አገልግሎት በልዩ ልዩ የብሄር/ብሄረሰብ ቋንቋዎች መስጠትና ፤ እንዲሰጥ ማድረግ ፤

፱. ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም ከተለያዩ የውጭ መንግስታት ጋር በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስክ ግንኙነት መመስረት ፤ ትብብር ማድረግና የልማት ስምምነቶችን መፈራረምና የስምምነቶችን አፈፃፀም መከታተል ፣

፲. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ማከናወኛ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም ከውጭም መንግስት በልዩ ልዩ መንገድ የተገኙና በጥቅል ለመንግስት የሚሰጡ የገንዘብ ፣ የማቴሪያልና ሌሎች ድጋፎችን ማስተዳደር ፤ አግባብ ላላቸው አካላት ማሰራጨትና አጠቃቀሙን መከታተል ፤

፲፩. በግል ተቋማት የሚከናወኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን ለማበረታታት በገንዘብ ፤ በማቴሪያል ፤ በሰው ሀይልና በተለያዩ መንገዶች ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣

፲፪. በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚሰማራ ብቃት ያለው የሰው ሀይል ለማፍራትና ያለውንም ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ ፣

፲፫. በትምህርት ፣ በምርምር ፣ ስርፀትና በምርት እንቅስቃሴ መካከል የእርስ በእርስ መደጋገፍ እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣

፲፬. በሳይንስና ቴክኖሎጂ የስራ ዘርፎች ላይ ለተሰማራ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሰው ሀይል የተሻለ የሥራ አካባቢና ማበረታቻ የሚፈጠርበትን ዘዴዎች መቀየስና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣

፲፭. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት አስተዋፅኦ ላደረጉ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማት ወይም ማበረታቻ መስጠት ፣

፲፮. ለኢትዮጵያ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለመፈለግ ፤ ለመምረጥ፣ ለመደራደር ፣ ለመግዛት ፣ ለማስገባት የሚያስችል አቅም መገንባትና ስርዓትን መዘርጋት ፤

፲፯. የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚያግዝ ፣ የፈጠራ ሥራዎችን ለተግባራዊነት እንዲበቁ የሚያበረታታና የፈጠራና መሰል ሥራዎች እንዲነቃቁና እንዲጐለብቱ የሚረዳ የፓተንት ስርዓት መዘርጋት ፤

፲፰. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚኖራቸው ማህበራት እንዲደራጁ የመርዳትና የማበረታታት እንዲሁም በሙያ ማኅበራት አማካኝነት የሚዘጋጁ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ነክ ፅሁፎችን ለሕትመት እንዲበቁና እንዲሰራጩ ድጋፍ መስጠት ፤

፲፱. በሀገር ውስጥ ርቀል የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻልና ለማሳደግ የሚደረጉ ጥናቶችንና የምርምርና ስርፀት ተግባሮችን ማበረታታትና ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ ፤

፳. የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃና ውጤቶችን ማሰባሰብና በአገር ውስጥ የተዘጋጁ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክንውኖችንና የምርምር ሥራዎችን የሚመለከቱ ጽሁፎችን ቅጅ በኮሚሽኑ የሚሰባሰቡበትን ሥርዓት መዘርጋት ፤

፳፩. የምርምርና ሥርፀት ተግባር ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችንና ድርጅቶችን የመመዝገብ ፤

፳፪. ሳይንስና ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ መሳተፍና መንግሥትን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ላይ ማማከር ፤

፳፫. እንደአግባቡ ትኩረት ባላገኙ ዘርፎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ከዋኝ ተቋማትን ማቋቋም ፤

፳፬. ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል ፤

፳፭. ውል መዋዋል ፣ መክሰስና መከሰስ ፤

፳፮. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣኑን ለሌላ የማዕከላዊ መንግሥት ተቋም በከፊል በውክልና መስጠት እና ፤

፳፯. አላማዎችን ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑና ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ተግባራት ማከናወን ፤

፮. የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ ፤

፩. ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት /ከዚህ በታች ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራ ፤

፪. በመንግሥት የሚሾም አንድ ኮሚሽነር ፣ አንድ ምክትል ኮሚሽነር እና

፫. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፯. የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ፤

፩. ጠቅላይ ሚኒስትር . . . . . . . . ሰብሳቢ
፪. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽነር . . . አባልና ጸሐፊ
፫. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር . . . አባል
፬. የጤና ጥበቃ ሚኒስትር . . . . . . . . »
፭. የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስትር . . . . . . . . . . . . . . አባል
፮. የኢንዱስትሪ ሚኒስትር . . . . . . . »
፯. የግብርና ሚኒስትር . . . . . . . . »
፰. የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትር . . . . . »
፱. የውጭ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር . . . »
፲. በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ . . . . አባል
፲፩. በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የሴቶች ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ . . . . . . . . . . . . አባል

፲፪· በኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒ ስትሩ የሚሰየሙ ሶስት (፫) ታዋቂ ባለሙያዎች . . . . . . . . . . . . አባል

፰· <u>የምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩ ታል፡

፩· የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ መቅረጽ፤

፪· በኮሚሽኑ አማካኝነት ተጠናቅረው የቀረቡ ዕቅ ዶችን መገምገምና ማጽደቅ፤

፫· ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የተጠየቀውን በጀት መመር መርና ለመንግሥት ቀርቦ እንዲጸድቅ ማድረግ፤

፬· የተለያዩ መመሪያዎችንና የሥራ ፕሮግራሞችን ማውጣት፤

፭· የራሱን የውስጥ ደንብ ማውጣት፤

፮· የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴና የየዘርፉን የሳይንስና ቴክ ኖሎጂ መማክርት ጉባኤዎችን መሰየም፤

፱· <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>

፩· ምክር ቤቱ አንድ መደበኛ ስብሰባ በየሶስት ወሩና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ልዩ ስብሰባ ያደርጋል

፪· ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፣

፫· በስብሰባ ከተገኙት ከግማሽ በላይ የደገፉት የው ሳኔ ሀሳብ የምክር ቤቱ ውሳኔ ይሆናል ። በስብሰባ ወቅት የአባላት ድምጽ እኩል ለእኩል ሲሆን ሰብ ሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ፤

፲· <u>የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· የብሔራዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት በሚያ ጸድቀው መመሪያና የሥራ ፕሮግራም መሰረት የኮሚሽኑን የዕለት ከዕለት ሥራ በበላይነት ይመ ራል ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋ ገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

ሀ) በጠቅላላ ሀገሪቱ በመንግሥት ድጋፍ ስለሚከና ወኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች እንዲ ሁም ስለኮሚሽኑ አመታዊ በጀትና የሥራ መርሀ ግብር የበጀት ዓመት ከመጠናቀቁ ሦስት ወራት ቀደም ብሎ ለምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፤

ለ) ሳይንስና ቴክኖሎጂን በሚመለከት ጉዳዮች ማዕከላዊ መንግሥትን ወክሎ በአለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ስብሰባ ላይ የመገኘት፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ የማድረግ፤

ረ) በመንግሥት ሰራተኞች ሕግ መሰረት የኮሚሽኑን ሰራተኞች የመቅጠር፤ የማስተዳደርና የማሰናበት፤

ሰ) ለኮሚሽኑ ስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ስልጣኑንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ሀላ ፊዎችና ሰራተኞች በውክልና የማስተላለፍ፡

ሸ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን የመወከል፤

ቀ) የኮሚሽኑን አላማዎችከግቡ ለማድረስ በምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን ።

## ፲፩. የምክትል ኮሚሽነር ስልጣንና ተግባር

ምክትል ኮሚሽነር

ሀ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ የኮሚሽኑን ተግባራት በበላይነት ይመራል፤

ለ) በኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## ፲፪. የዘርፉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መማክርት ጉባኤዎች፤

ጉባኤዎች በኮሚሽኑ የዘርፍ መምሪያ ሀላፊዎች ጸሐፊነት የሚመሩ በየዘርፉ የሚታቀፉ የተለያዩ ተቋማት ተወካዮች፤ ግለሰብ ባለሙያዎች ሆነው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል።

፩. የዘርፉን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች የመገምገም፤

፪. ስለዘርፉ ዕቅድና ትኩረት የሚገባቸውን ፕሮጀክቶች መጠቀም፤ ማማከር

፫. የዘርፉን ዕድገትና እንቅስቃሴ በተመለከተ ፖሊሲ እንዲዘጋጅ የማድረግ፤ የመምከርና የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፤ ሲፈቀድም በተግባር መተርጐሙን መከታተል፤

፬. በዘርፉ በምርምር በስርጸትና በተጠቃሚው ክፍል የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ተስማሚ ስርዓት መዘርጋት፤

፭. በዘርፍ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን ከፖሊሲ ትኩረት አኳያ ቅደም ተከተላቸውን የመወሰን፤
ድጋፍ ሊሰጣቸው የሚገባውን ፕሮጀክቶች ለውሳኔ ማቅረብ።

## ፲፫ በጀት

፩. የኮሚሽኑ የገንዘብ ምንጮች ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፤

ሀ) ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፤

ለ) ለኮሚሽኑ ከሚሰጡ እርዳታዎችና ድጋፎች

መ) ሌሎች ምንጮች

፪. ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ብሔራዊ ባንክ በሚወክለው ባንክ ተቀማጭ ሆኖ ለኮሚሽኑ አላማዎች ማስፈጸሚያ ይውላል።

## ፲፬. ስለሂሳብ መዝገብ

፩. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል።

፪. ኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብቱን ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል።

## ፲፭. ስለመመዝገብ

በብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት አማካኝነት የሚወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የምርምርና ስርፀት እንዲሁም ሌሎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ የስራ መስክ ወይም ከዚህ ጋር በተያያዙ የምርምርና ስርጸት ተግባር ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ወይም ድርጅት በኮሚሽኑ መመዝገብ አለበት።

**፲፯. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ወይም ድርጅት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

**፲፰. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች**

፩. የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽንን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፪/፲፱፻፷፯ /እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ።

**፲፱. መብትና ግዴታ ስለመተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር ፷፪/፲፱፻፷፯ ዓ.ም የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ መሰረት ለተቋቋመው ኮሚሽን ተላልፍዋል ።

**፳. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ. ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

ፕሬዚዳንት